# የለመደ መደመደ

ከበልጂግ አሊ

ስለ ቀይ ሽብር ብዙ ነገሮች ይፃፋሉ። እስከ አሁን ድረስ እኔ ለቀይ ሽብር ተጠያቂ ነኝ ብሎ የወጣ የለም። ወያኔም ቀይ ሽብርን የኢሰፓዎች ማስፈራሪያ አደርጎ ተጠቀመበት እንጂ ሃቁና የተገኙትን ዶክመንቶች ለህዝብ ይፋ አላደረገም። ማን መቼ ማንን እንገደለ፣ እንደገረፈ፣ ከነፎቶአቸው ቢወጣ የተቃዋሚዎች ጎራ ቁጥር ሊሳሳ እንደሚችል አልጠራጠርም።ሰሞኑን በፓልቶክ የደርግ ቀንደኛ የነበረችው ብዙ ወንድምአገኘሁ ስለኢሕአፓ ተንገፍግፋ ስትናገር ስስማት ድሮ በየቀበሌውና በየሬድዮኑ ቀይ ሽብር እንዲፋፋም የምታደርገውን ቅስቀሳ የተቀዳው እንደገና አሁን ለማቅረብ ቢቻል ኖሮ ምን ያህል የሰው ልጅ ቆዳውን የሚቀያይር እስስት ሊሆን እንደሚችል ለማሳየት ይቻል ነበር።ዛሬ ወያኔ ከወደቀ ለኔም ስልጣን ይገባኛል ባዮች በደርግ መንግስት ስር በመሆን የሰሩትን ወንጀል በመካድ እኛ አደለንም እነርሱ ናቸው በመባባል ላይ ይገኛሉ። በዛ ወቀት ለተገረፍን ፣ ለተገደልን ፣ለተሰቃየን፣ግን ማን እንደገረፈን፣ ማን እንዳሰቃየን፣ ማን እንደገደለን ፣ ሰለምናወቀው ልዩነቱ ለኔ በበኩሌ ብዙ አደለም። እኛ የለንበትም የሚለውን ክህደት ግን የለመደ መደመደ ብዬ አልፈዎለሁ ።

የዛሬን ፅሁፌን ለማቅረብ የገፋፋኝ በባንዳ ሞላ ዘገዬ ጥር13 ቀን 1999 በሪፖርተር ላይ የቀረበው ቃለመጠይቅና የካቲት 25 በገብረእግዚአብሔር ተስፋዬ የተሰጠው መልስ በሚመለከት ነበር። ሁለቱም ከፋሽሽቱ መንግስት ወግነው ነበሩ ሲሆን አሁን በጣም ሊያስማማቸው ያልቻለው ዳሮ ነጋሽን የገደው ግርማ ከበድ የመኢሶን አባል ነው ወይስ አደለም የሚለው ነው። ነገሩ ቀላልነት ያለው ይመስላል።ግን አደለም በሃገራችን ከተሰሩት ግፎች ውስጥ በአስቃቂነቱ ከሚታወቁት አንዱ ነው።

ሞላ ዘገዬ ማን ነው?

በተደጋጋሚ እንደጠቀስኩት በአሁኑ ግዜ ከወያኔ ጋር የሚሰራ ሲሆን አሁንም ቢሆን ፋሽሽታዊ አመለካከቱ ያልተቀየረና የአብዬታው ሰደድ አባልና የደርግ አባል ፣ የመላኩ ተፈራ የቅርብ ጓደኛ ነው። በአለፈው ግዜ ሲቪሊቲ በመባል በሚታወቀው የወያኔ ፓልቶክ ክፍል ስለ ህግ የበላይነት ለወያኔ ደጋፊዎች ለማስረዳት ቀርቦ እንደነበረ ይታወሳል ። ግለስቡ የሚለው በአጭሩ

***ሪፖርተር፡- የጎንደሩ ሻለቃ መላኩ ተፈራ፣ የጉራጌው አቶ ገስግስ ገ/መስቀል፣ የአዲስ አበባ አራት ኪሎው አቶ ግርማ ከበደና የመሣሰሉት፡፡ እነዚህ የተሾሙት በደርግ ባለሥልጣናት ነው፡፡ አቶ ገስግስ በሻለቃ ካሣዬ አራጋው ተመርጦ ነው የጉራጌን ሕዝብ የጨረሰው…፡፡ እነዚህን እንዴት ደርግ አያውቃቸውም ማለት ይቻላል?***

***አቶ ሞላ፡- ድርጅቱ በሚያውቃቸው ላይ ዝም ይላል፡፡ በማያውቃቸው ላይ ግን እርምጃ ይወስዳል፡፡ ግርማ የሰራው አሰቃቂ ተግባር ደርግ ጽ/ቤት ቀረበ፡፡ የመኢሶን አባል ነበር፡፡ አሁን ግን አባላችን አልነበረም ብለው ይክዳሉ፡፡ ሊቀየሙኝ ይችላሉ፡፡ እኔ ግን እውነት እናገራለሁ፡፡ በጊዜው የምናውቀው አባል እንደነበር ነው፡፡ በኋላ በደርግ ውሳኔ ነው የተገደለው፡፡ የመኢሶን አባላት አብዛኛዎቹ እንዳኮረፉ አውቃለሁ፡፡ እኔና ሻለቃ መላኩ ክብር ዘበኞች ነን፡፡ ደርግ ከመሆናችን በፊት ለረዥም ጊዜ እንተዋወቃለን፡፡ አለቃዬ ነበሩ፡፡ በደንብ አውቃቸዋለሁ፡፡ ተፈፀመ የተባለውን ድርጊት ሻለቃ መላኩ በምን ዓይነት ሁኔታ***

*እንደፈፀሙት አላውቅም:: መንግሥት አያውቀውም ማለት ግን አልችልም:: መንግሥት ያወቀዋል::*

*«በደርግ ዘንድ ተሰሚነት ያላቸው የዚያ አካባቢ ተወላጆች አቤት ብለው ሕዝብ እያለቀ ነው፤ ወጣቱ እየተሰደደ ነው፤ ሻለቃ መላኩ እንዲህ ዓይነት ነገር እየሰሩ ነው በማለታቸው ለወቀሣ ተጠርተው እንደነበር በደንብ አስታውሳለሁ:: የሚያጣራ ቡድን ተልኮ በምስጢር አጣርቶ መጥቷል:: የተወሰደ እርምጃ ግን አልነበረም::*

እንግዲህ ወያኔ በየሚዲው የሚያቀርበው ይህንን ግለስብ ነው።የጨነቀው እርጉዝ ያገባል ማለት ይህ ነው። ይህ ፋሽሽት የደርግ አባል እንደለመደው በጥቅም ተገዝቶ ለወያኔ ጠበቃ ቆሞ በየቦታው የወያኔን ዴሞክራሲዊነት ይሰብካል ።ስለዚህ ግለሰብ እንደገና እመለስበታለሁ።

ለዚህ መልስ ደግሞ ገብረእግዚአብሔር ተስፋዬ የመኢሶን አባል የነበረ በዛው በሪፖርተር ላይ የሰጠውን መልስ ባጭሩ እንመልከት

*«በመኢሶን ላይ ብዙ የሃሰት ፕሮፖጋንዳዎች ተሰራጭተዋል:: ቀደም ሲል በኢሕአፖ አመራር፣ ቀጥሎም በሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ይመራ በነበረው መንግሥትና አሁን ደግሞ በአንዳንድ የኢሕአዴግ አመራር አባላት የሃሰት ፕሮፖጋንዳው አሁንም ቀጥሏል:: ከሞት የተረፍን አለንና እውነቱን ዕድል በተገኘ ቁጥር ለሕዝብ ከማሳወቅ ወደ ኋላ አንልም:: በተከታታይ መንግሥታት የተነዛን ፕሮፖጋንዳ ማስተባበል አዳጋች እንደሆነ አልዘነጋሁም:: ሆኖም ግን ጉዳዩን ዝም ብሎ ማሳለፍ የወንጀሉ ተባባሪ የመሆን ያህል ተሰማኝ::*

*«እርስዎ ግርማ ከበደ የመኢሶን አባል ነው የሚሉት፣ በወቅቱ በነሻለቃ ወልደማርያም በወታደራዊ ካድሬዎች ውስጥ ዓላማ ያለው የፖለቲካ አሉባልታ በማሰራጨት በታወቀው ቡድን መኢሶንን ለማስጠላት ታቅዶ የተነዛውን አሉባልታ ይዘው ይመስለኛል:: ግርማ ከበደ ግድያውን የፈጸመው በመኢሶን በታዘዘው መሰረት ቢሆን ኖሮ ግርማ በምርመራ ወቅት መኢሶን ነው ያዘዘኝ ማለት ይችል ነበር:: ብሎ ቢሆን ኖሮ እርስዎ የምርመራ ቃሉን በማስረጃነት ያቀርቡልን ነበር ብዬ እገምታለሁ:: መኢሶንም በወቅቱ በዚህ ጉዳይ የተነሣ የተወቀሰውም ሆነ የተከሰሰበት ጉዳይ አለመኖሩን እርስዎም ጠንቅቀው ያውቁታል::*

*«መኢሶን ግርማ ከበደ አባሌ አይደለም ብቻ ሣይሆን ያለው፣ የእነ ለገሰ አስፋው እጅም ከግርማ ከበደ በስተጀርባ መኖሩንም አጋልጧል:: ይህንን አርስዎ በወቅቱ አያውቁም ነበርን? ስለዚህ ጉዳይ መኢሶን ሐምሌ 1981 ዓ.ም ላይ ሂሣዊ ግምገማ ሲያደርግ ስለ ግርማ ከበደ ያለውን እንመልከት:: «የዚህን ሰው መታጠቅ በሚመለከት መኢሶን እንዲያውም በተጻራሪው ግርማ ከበደ የቦዘኔ ባህሪይ የሚታይበት አደገኛ ግለሰብ መሆኑን በማስገንዘብ ግርማ ከበደ በግል እንዳይታጠቅ አስተያየቱን ለሚመለከተው ክፍል ሰጥቶ ነበር:: በተለይ ለገሰ አስፋው ይህንን የመኢሶንን አስተያየት በመቃረን ግርማ ከደበን በግሉ ክላሽንኮቭ አስታጠቀው:: ክላሽንኮቭ ማስታጠቅ በወቅቱ ለየትኛውም የቀበሌ ማኅበር መሪ የተደረገ አልነበረም::*

*«በዚህ አብዮታዊ ሰደድና የለገሰ አስፋው ድጋፍ የልብ ልብ የተሰማውና የተማመነው ግርማ ከበደ፣ ከግብረ አበሮቹ ጋር ሆኖ በግሉ የሞት ብያኔ እየሰጠ በማን አለብኝነት ግድያዎችን ፈጸመ» ነው የሚለው:: የመኢሶንን ሂሳዊ ግምገማ 1981 ዓ.ም ገጽ 18ን ይመልከቱ:: ከእርስዎ ምስክርነት የተረዳሁት ነገር ቢኖር መጋቢት 1969 ዓ.ም. የተጀመረው የወዝ/ሰደድ ፀረ መኢሶን ፕሮፖጋንዳ እስካሁን መቀጠሉን ነው:: እርስዎ የደርግ ባለሥልጣናት የሕግ አማካሪ ነዎትና እስቲ ሻምበል ለገሰ አስፋውን፣ ግርማ ከበደን ማን አስታጠቀው ብለው ይጠይቋቸው:: በፈጸሙት ጥፋት ከልብ ተጸጽተዋል ብለዋልና እውነቱን*

*የሚነግሩዎት ይመስለኛል:: መኢሶን በወቅቱ በሕጋዊም፣ በሕገ ወጥም መንገድ የሚታገሉ አባሎቹን አሰማርቶ ነበር:: በሕጋዊ መድረክ ላይ ያሰማራቸውን አባሎች እርስዎም መንግሥትም ያውቃቸዋል ብዬ እገምታለሁ:: በህቡዕ የሚታገሉትን አባሎች ግን እንኳን እርስዎ እኔም አባል የነበርኩት አላውቃቸውም:: መኢሶን ደግሞ ግርማን አባሌ ነው ብሎ እንዳላስመዘገበው እርስዎም ያውቁታሉ::*

*„የመኢሶን አባል ነው ሲሉ ምን ማስረጃ አግኝተው ነው? ሌላው አስገራሚ ጉዳይ ደግሞ «ግርማ የሰራው አሰቃቂ ተግባር ደርግ ጽ/ቤት ቀረበ::. . . በኋላ በደርግ ውሣኔ ነው የተገደለው» ያሉትን ነው:: እውን ደርግ ግርማ ከበደ ላይ ያንን እርምጃ የወሰደው ለፍትሕ በመቆርቆር ነው? ለምን እውነቱን ይደብቃሉ? መኢሶኖች ጨፍጫፊዎች፣ ደርጎች ግን ለሰው ሕይወት ደንታ ነበራቸው ሲሉ አያፍሩም:: እውነት ደርግ የሰው ሕይወት አለ ፍርድ አግባብ ሲጠፋ ቢቆረቆር ኖሮ ቀይ ሽብር የሚባል በአገራችን ይካሄድ ነበር? ደርግ ለፍትሕ ደንታ ቢስ እንደሆነ ማናችንም እናውቃለን::*

እዚህ ሁለት የደርግ ባለስልጣናት የሚሉትን ስንመለከት ምን ያህል በግርማ ከበደ ላይ እንኳን መስማማት እንዳልቻሉ ያሳየናል።በዛው ተመርኩዘው እውነቱን ለነርሱ እንደሚመቻቸው ለመቀያየር እንደሚጥሩ ነው የምንመለከው። ዋናው ቁምነገሩ ግን መኢሶን አልነበርኩበትም የሚለውን ለመከታተል ጥረት አድርጌ የቆየ ዶክመኝቶችን አገላብጫ ነበር። ለመሆኑ ገብረእግዚአብሔር ተስፋዬ ስለ መኢሶን መሰወር ያቀረበው አሳብ በአጭሩ እንመልከት፦

*„መኢሶን ከደርግ ተሸሽጎ ነሐሴ 14 ቀን 1969 ዓ.ም በወዘደሩና በገበሬው መሃል መሰወሩ ይታወቃል:: የሩቅም ሆኑ የቅርብ ሰነዶች ይህንን ይመሰክራሉ:: ቀይ ሽብር የተካሄደበትን ድርጅት ቀይ ሽብር አካሂዷል ማለትን ምን አመጣው? አቶ ሞላ በወቅቱ የትግል ጓዶቼ የሚሏቸው ግለሰቦች ይነዙ ስለነበሩ ሌሎች አሉባልታዎች «ነበር» በሚለው በዘነበ ፈለቀ በተፃፈው መጽሐፍ ያንብቡ:: በሰደድ ውስጥ የሃሰት ፕሮፖጋንዳ የሚነዛ ቡድን ተቋቁሞ እንደነበር ይረዱልኛል::*

አሁን የሁለቱን ክርክር ለማወቅ የፈለገ ሰው አንድ ነገር ሊገነዘብ ይገባል። ሁለቱም የደርግ በለስልጣናት እንደሚዋሹት ሳይሆን ሃቁን እንመልከት።ለኔ ዋቢዬ ነው ብዬ የማቀርበው የሰፊው ሕዝብ ድምፅ የመኢሶን ልሳን የሆነውን ሐምሌ 15ቀን 1970 የወጣውን ነው። የሚገርመው ግን ያኔ ይጣሉ የነበሩት አንተ ትንሽ ነው የገደልከው እኔ ብዙ ነው የገደልኩት በማለት የገዳይ ሻንፒዮን ለመሆን ነበር።

ጋዜጣው „መኢሶን ከሕብረቱ ስለመወገዱ“ የሚል እርዕስ ይዞ ነበር የወጣው ። በጋዜጣው መግቢያ የተፃፈው ላይ ለሁላችንም ሳያስደንቀን አይቀርም።ገና በአንድ ወር ተረሳ የተባለው ታሪክ ዛሬ ምን ያህል ሊወላገድ እደሚችል መገመት ይቻላል።

*ገፅ* 1

1. *መግቢያ*

*„ ይገርማል! አንደንድ ሰዎች ወሮች አልፈው ወሮች ሲተኩ ነገሮችን የመርሳት ዝንባሌ አላቸው። ነገር ግን ደግሞ ከሁሉም ነገር ይልቅ በቅድሚያ ለመርሳት የሚፈልጉት እራሳቸው ተጠያቂ የሚሆኑባቸውን ጉዳዮች ነው። ከህሊናቸው ጋር ለማስታረቅ የሚያስቸግራቸውን ጉዳዮች ነው። ስለዚህም፣ የማይፈልጉት ምክንያት፣ የማይፈጥሩት ሰበብ፣ እራሳቸውን ለማታለል የማያደርጉት ጥረት የለም።ጉድጓዶችን*

*እየቆፈሩ እራሳቸውን ለመቅበር ፣ ግድግዳዎችን እየገነቡ ከበስተጀርባቸው ለመሸሸግ ፣ ከዛም በለው ህሊናቸውን „ለማሳረፍ“... ሊያሌ አስደናቂ ጥረቶችን ያሳያሉ“።*

አንባቢያንን የምጠይቀው ይህንን ፅሁፍ ልብላችሁ እንድታነቡልኝ ነው። እስቲ እነ ብዙ ወንድምአገኝ ይህንን ከቀድሞ ድርጅታቸው የተሰጠውን ይመልከቱት።ለመሆኑ ኢሕአፓን ባልሆነ መወንጀልና አንዳንድ እውነቱን የማያውቁትን በማወናበድ የህሊና እረፍት ይሰጣቸው ይሆን። ለሰራችው ወንጀል ድርጅት እየቀያየረች ስለ ኢሕአፓ መጥፎ ነገር ማውራት ያለባትን የመንፈስ ጭንቀት ሊያስወግድላትም።

በዚሁ ጋዜጣ ላይ ገፅ 1 ላይ ወደ መጨረሻው ላይ

*„ኢማሌድህ „ መኢሶን ከኢማሌድህ አባልነት ተሰረዘ“ በማለት „ ከህብረት ድምፅ „ |ሐ.ድ ቅ.1 ቁ.4 ሚያዚያ 1970 ልሳኑ ያወጣውን ጸሁፍና ውሳኔ ስንመለከት በመጀመሪያ የተገነዘብነውን ከዚህ በላይ የተናገርነው እውነት ነው“።*

እንግዲህ ይህንን ከአየን መኢሶን የተባረረው ሚያዚያ 1970 ዓ.ም እንጂ ገብረእግዚአብሔር ተስፋዬ እንዳለው መኢሶን ከደርግ የተሸሸገው ነሐሴ 14 ቀን 1969 ዓ.ም አደለም። የመኢሶን መዋቅር እስከ ሚያዚያ 1970 ዓ. ም. ድረስ በመዋቅሩ ውስጥ ነበር ማለት ነው። ስለዚህም „መኢሶን የቀይ ሽብር ሰለባ ነው“ የሚለው የወቅቱ አስቂኝ መፈክር ሊሆን ነው የሚገባው።

እንደማንኛውም ሰው መኢሶን ከህብረቱ ለምን ወጣ ብላችሁ ትጠይቁኝ ይሆናል። ታዲያ የበልጅግ አሮጌ አጥንት ለቀኑ ኮምፒውተር ላይ መቀመጥ የሚፈቀድለት ጊዜ ስለደረሰ በሚቀጥለው መልሱን ይገኙ እቀርባለሁ።

ሰለኛ የሚያስብ በሰላም ይክረም

በልጅግ አሊ